በሃገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣
ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣

# የሁለተኛ ዓመት
# የሥራ ክንዉን ዘገባ

በኢፌዲሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ

**FDRE Attorney General**
**Legal and Justice Affairs Advisory Council**



# ማውጫ

1. መግቢያ ..... 2
2. የአማካሪ ጉባኤው አወቃቀር ..... 3
3. አማካሪ ጉባኤው ያስገኛቸው ውጤቶች በአጭሩ ..... 4
4. በጉባኤው ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተሰጡ መፍትሄዎች ..... 7
5. የጉባኤው የሥራ ቡድኖችና የጽ/ቤቱ አባላት እና ሌላ በጎ ፈቃደኞች ዝርዝር ..... 8

# 1. መግቢያ

ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ በሚያዝያ 2010 ዓ.ም ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ መንግስታቸዉ የተለያዩ ሥር-ነቀል የለውጥ እርምጃዎችን እየወሰደ እየወሰደ እንደሆነ ይታወቃል። በሕግና ፍትህ ዘርፍ ውስጥ ከተተገበሩት አፋጣኝ የአጭር ጊዜ እርምጃች ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ እስረኞችን በይቅርታና ምህረት መልቀቅ፤ በመገናኛ ብዙሃንና በበይነመረብ ላይ የነበሩ ገደቦችን ማንሳት፤ በሽብርተኝነት የተፈረጁ የፖለቲካ ድርጅቶችን ከሽብርተኝነት መዝገብ ማዉጣት፤ በስደት የነበሩ ጋዜጠኞችን፣ የማህበረሰብ አንቂዋችን እና የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትን ወደ ሀገራቸዉ እንዲገቡ መፍቀድ በዋነኝነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። መንግስት የነዚህን እርምጃዎች ዘላቂነት የሚያረጋግጡ የህግና የፍትህ ስርዓት ለውጦችንም እንድሚያከናውን ቃል ገብቷል። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መስርያ ቤት ይህን ቃል ለመጠበቅ ብሎም በሕገ መንግስቱ የተቀመጡትን የፍትህ ራእይ ለማሳካት ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ የሕግና ፍትሕ ሥርዓት ለውጥ ሂደት ሲሆን፤ 13 አባላት ያሉትን የሕግና ፍትህ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔን አቋቁሞ የለውጥ ስራው በፍጥነት እንዲጀምር አድርጓል።

> **ዓላማ**
>
> *የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔ ዋና ዓላማ የኢትዮጵያ መንግስት የፍትሕ አቅርቦትና ተደራሽነትን ለማሻሻል፣ የሕግ የበላይነትን ለማስከበር፣ ሰብዓዊ መብቶችን ለመጠበቅና እዉነተኛ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሀገር ለመገንባት የሚያደርገዉ ጥረት ዉጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ከፍተኛ ጥራት ያለው የህግ ምክር እና አገልግሎት መስጠት ነው።*

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሀገራችን ያለችበትን የለውጥ ሂደት ውጤታማነት ለማረጋገጥ እየወሰዳቸው ያሉ የተለያዩ የተቋማትና የሕግ ማሻሻያ ሥራዎች ዓላማ በሃገሪቱ የመጣው አዎንታዊ ለውጥ ተጠናክሮ ኢትዮጵያ የሕግ በላይነትና ፍትህ የሠፈነባት፣ ሰብዓዊ መብቶች የተከበሩባት፣ በዲሞክራሲያዊ አግባብ የምትመራ ሀገር መገንባት ነው። የሕግና ፍትህ ጉዳዮች አማካሪ ጉባዔው ሥራና ተግባር ይህ ዓላማ በሙያዊ፣ ተቋማዊና፣ በጥናት በተደገፈ መንገድ እንደሚሰራ ማረጋገጥ ነው። አማካሪ ጉባዔዉ የሰብዓዊና ዴሞክራሲ መብቶችን እንዲሁም የሕግ የበላይነትና ተያያዥ ሕገ-መንግስታዊ መርሆዋች መሰረት በማድረግ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን በሕግና ፍትሕ ማሻሻያ ጉዳዮች ላይ የማማከር ሃላፊነት የተሰጠዉ ሲሆን የአማካሪ ጉባዔዉ ስልጣንና ተግባራት በዋናነት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

- በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ተቋማት ዉጤታማነት ላይ ተፅዕኖ ባላቸዉ ሕጎች፣ ተቋማትና አሰራሮች ላይ ጥልቅ የሆነ ጥናትና ግምገማ ማድረግ፤
- ተጠያቂነት የሰፈነበት የመንግስት አስተዳደርንና የሕግ የበላይነትን ለማስፈን እንዲሁም ሕገ-መንግስታዊ መብቶችን ሙሉ በሙሉ ለማረጋገጥ በሚደረገዉ ጥረት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን መለየት፣ ማጥናትና መሰብሰብ፤
- ሕጋዊና ተቋማዊ ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ አይነታዊ (ገላጭ) የጥናት ውጤቶች ላይ መሠረት ያደረጉ የማሻሻያ ሀሳቦችን፣ እና በተጠኑና በፕሮግራም በተደገፉ እዉነታ ላይ የተመሰረቱ የማሻሻያ ፓኬጆችን ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቅረብ።

አማካሪ ጉባዔዉ ተግባሩን በሚገባ መወጣት ይችል ዘንድ የለት ከዕለት የአስተዳደር ሥራ የሚያከናዉን ጽሕፈት ቤት ያቋቋመ ሲሆን፤ የሕግና ፍትህ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ቴክኒካዊ ስራዎቹን የሚያከናውኑ የሥራ ቡድኖችንም መስርቷል። እያንዳንዱ

የሥራ ቡድን በተለያዩ ሕጎችና አሰራሮች ላይ ጥልቅ ጥናት በማድረግ የማሻሻያ ሀሳቦችንና ረቂቅ ህጎችን ለመንግስት ያቀርባል። አማካሪ ጉባዔው እና ያቋቋማቸው የሥራ ቡድኖች በትምህርት ደረጃቸው የላቀ ደረጃ ላይ የደረሱና በሙያቸው አንቱ የተባሉ የሕግ፣ የሲቪል ማህበረሰብ፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የሰብዓዊ መብት እና የዲሞክራሲ ዘርፍ ባለሙያዎችን ያካተቱ ናቸው። እነዚህ ባለሙያዎች በዋናነት በበጎ ፈቃደኝነት የሚያገለግሉ በመሆኑ አገሪቷ የሚያስፈልጓትን የሕግና የፍትህ መዋቅር ማሻሻያዎች ያለ ክፍያና በከፍተኛ ሙያዊነት፣ ብቃትና ውጤታማነት እንድታከናውን ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ።

## 2. የአማካሪ ጉባኤው አወቃቀር

አማካሪ ጉባኤው የሕግና ፍትህ ጉዳዮች ለውጥ ስራውን በሰባት ንዑስ ፕሮግራሞች ከፍሎ ወደ ስራ የገባ ሲሆን እነዚህም የፍትሕ ማሻሻያ፣ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ፣ የፍትሐ ብሔር እና የንግድ ሕግ ፣ የዴሞክራሳዊ ተቋማት፣ የሕግ እና ተዛማጅ አገልግሎቶች፣ የሕግ ማውጣት ሂደት እና የአስተዳደር ሕግ፣ የሕግ ሥልጠና እና ትምህርት ንዑስ ፕሮግራሞች ናቸው። አማካሪ ጉባዔዉ የተቋቋመበትና የተዋቀረበት መንገድ በማሻሻያ ሂደቱ በኢትዮጵያና በዉጭ ሀገር የሚገኝን ልምድና እዉቀት በመጠቀም በስምንት የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ መንግስትን ለማማከር ሲሆን የጉባኤው አወቃቀር በቻርት (ኦርጋኖግራም) ተመስሎ እንደሚከተለው ቀርቧል:-




የአማካሪ ጉባኤው ዋና አካላት ስራዎችና ተግባራት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው:-

### አማካሪ ጉባኤው

- የሕግና ፍትህ ስርዓት ለውጥ ሥራው የሚመራበትን ፍኖተ ካርታ አዘጋጅቶ አፅድቋል፣
- የጉባኤውን ሥነ-ስርዓት ደንብ አዘጋጅቶ አጽድቋል፣
- የህዝብ ተሳትፎ ስትራቴጂ ሰነድ አዘጋጅቶ አጽድቋል፣
- የሥራ ቡድኖችንና ጽ/ቤቱን አዋቅሮ ሥራቸውን እየተከታተለ ይገኛል፣
- የራሱን፣ የጽ/ቤቱንና የሥራ ቡድኖችን አሰራር ሥነ-ስርዓት፣ የሥነ-ምግባር ደንብ የስራ መርሀ-ግብሮችና የሚጠበቅባቸውን የጥራት ደረጃ አስቀምጦ ይከታተላል፣

## የሥራ ቡድኖች

- የሥራ ቡድኑን መርሀ-ግብር፣ የርዕሰ ጉዳይና የኃላፊነት ወሰን ሪፖርትና የሥራ እቅድ አዘጋጅተው በአማካሪ ጉባኤው ያጸድቃሉ፣
- የተቋቋሙበትን ዘርፍ በሚመለከት የዳሰሳ ጥናት በማዘጋጀት በአማካሪ ጉባኤው ያጸድቃሉ፣
- የዳሰሳ ጥናታቸው የተቀመጡ የውሳኔ ሃሳቦችን በመተግበር በተለይም የሕግ ማርቀቅ ስራዎችን በማከናወን በአማካሪ ጉባኤው ያጸድቃሉ፣
- የጸደቁ ህጎችን ለህዝብና ለባለድርሻ አካላት በማቅረብ ያወያያሉ፣ ግብዓቶችንም በመውሰድ ረቂቅ ህጎችን ያዳብራሉ፣
- ረቂቅ ህጎች በሕግ ማውጣት ሂደት በሚያልፉበት ጊዜ ሁተታ ዘምክንያት በበጻፍ እንዲሁም በሚኒስቴሮችና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መዋቅሮች በመቅረብ ያስረዳሉ ጥያቄዎች ይመልሳሉ፣
- ሕጎችና ሌላ የለውጥ ሃሳቦች አተገባበር ላይ ለመንግስት የተለያዩ ምክርና ድጋፍ ያቀርባሉ፣

## ጽ/ቤቱ

- የአማካሪ ጉባኤውን አስተዳደራዊ ግዲታዎች ጉባኤው በሚያስቀምጠው አቅጣጫና በጉባኤው ሰብሳቢ መሪነት ይወጣል፣
- የገንዘብና የነጻ አገልግሎት ድጋፍ ወይም ሌሎች ትብብሮችን በሃገር ውስጥና ዓለማቀፍ ደረጃ ያፈላልጋል ግብዐት ያድርጋል፣
- የሀገር ዉስጥና ዓለም አቀፍ ባለሙያዎችን እንዳግባብነቱ እየመለመለ በፈቃደኛ ሰራተኝነት በቅጥር ወይም በአማካሪነት ውል መሰረት እንዲያገለግሉ ያደርጋል፣
- የአማካሪ ጉባኤው ያጸደቃቸው የለውጥ ፍኖተ ካርታ፣ ሥነ-ስርዓት ደንቦች፣ ስትራቴጂዎች ወዘተ መተግበራቸውን በመከታተል ለጉባኤው ሪፖትቶች ያቀርባል፣
- በአማካሪ ጉባኤው፣ በሥራ ቡድኖች፣ በጠቅላይ ዓቃቢ ሕግና በሊሶች አካላት መሃል ያሉ ግ ንኙነቶችን ያሳልጣል፣
- ድረ-ገፅ፣ ኢሚል እና ድራይቭ አካዉንቶች ከፍቷል፣
- የአማካሪ ጉባኤውንና የሥራ ቡድኖችን ስብሰባዎችና ሕዝባዊ ምክክር መድረኮች ያመቻቻል፣

## 3. አማካሪ ጉባኤው ያስገኛቸው ውጤቶች በአጭሩ

ለዴሞክራሲያዊነትና ሰብዓዊ መብቶች መከበር ትኩረት የሰጠዉ የሕግና ፍትሕ ሥርዓት ማሻሻል ሂደት አለማቀፍ ደረጃዎችን የጠበቀና በጥሩ ተሞክሮዎች የታነጸ እንዲሆን አማካሪ ጉባኤው ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ይህን ለማረጋገጥ አማካሪ ጉባኤው አሳታፊና ገለልተኛ የሆኑ አወቃቀሮችን፣ የጥናትና የሕግ አወጣጥ ፖሊሲዎች ዘዴዎችና አሰራሮች ዘርግቷል። እነዚህ አወቃቀሮችና አሰራሮች አለም አቀፍ ደረጃዎችን በሃገራችን ከመተግበርም አልፈው የሃገር ውስጥ ልምድና እዉቀትንም ያማከሉ ናቸው። እንደ ኒው ዮርክ ዩኒቨርሲቲ፣ ፓዝፋይንደር ኢንተርናቲአናል፣ እና የተባበሩት መንግስታት የአስተያየት እና ሀሳብን የመግለጽ መብት ልዩ ዘጋቢ ያሉ አካላት “መሪ ብርሃን” (Beacon)፣ “አስደናቂ”፣ “ግሩም”፣ “ያልተጠበቀ አካታችነት የሚታይበት” ሲሉ አወቃቀሮቹን አወድሰዋቸዋል። የአማካሪ ጉባኤው ባለሙያዎችም "ቁርጠኝነት [ያላቸው] ባለሙያ[ዎች]" መሆናቸው ባለማቀፍ ደረጃ ተመስክሮላቸዋል።

> **ፓዝፋይንደር ኢንተርናሽናል**
>
> *“በፖለቲካ ሽግግር ውስጥ ላሉ ሌሎች አገሮች እንደ ምርጥ ተሞክሮ ሊወሰድ ይችላል።”*
>
> **የተባበሩት መንግስታት ልዩ ዘጋቢ**
>
> *“በዓለም ዙሪያ ላሉ ዴሞክራሲያዊ ሂደቶች አርአያ መሆን ያለበት አሰራር ነው”*
>
> *“የአሰራር ዘዴዎቹ በአካባቢውና ከዛም ባለፈ ላሉ ሃገራት በአርአያነት ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው።”*

ከዚህም በተጨማሪ እነዚሁ ተቋማት የአማካሪ ጉባኤው አወቃቀሮች ዘዴዎችና አሰራሮች በዓለማቀፍ ደረጃ በሞዴልነት ተወስደው በሌላ ሃገራት ሊተገበሩ እንደሚገባ ደምድመው ይህንኑ በተለያዩ ዓለማቀፍ መድረኮች ማንጸባረቅ ከጀመሩ የሰነበተ

ሲሆን በአማካሪ ጉባኤው የተዘጋጁ ጥናቶችና የተረቀቁ ሕጎችም በአለማቀፍም ሆነ በኢትዮጵያ የሕግ ምሁራን ከፍተኛ ተቀባይነትን እንዳገኙ ይታወቃል።[1] አማካሪ ጉባዔዉና የሥራ ቡድኖቹ ከፖለቲካዊ ፍላጎት ይልቅ ነፃነትን፣ ሙያዊነትን፣ ሙያዊ ስነ-ምግባርንና የአባላቱን ልምድና ሕሊና መሠረት በማድረግ በማሻሻያ ሂደቱ ዉስጥ የመሪነት ሚና ይጫወታሉ።

የአማካሪ ጉባኤው ፕሮግራሞች፣ ንዑስ ፕሮግራሞችና በውስጣቸው የሚካተቱ ሥራዎች ውስጥ አፋኝና ለሰብዓዊ፣ ዴሞክራሲያዊ እና ሕገ-መንግስታዊ መብቶች መከበር እንቅፋት የነበሩ እንደ ፀረ ሽብር፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የፖለቲካ ፓርቲ እና የበጎ አድራጎትና ማህበራት ሕጎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲሻሻሉ ተደርጓል። አማካሪ ጉባኤው ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ያከናወናቸዉ ዋና ዋና የሕግና ፍትህ ስርዓት ለውጥ ውጤቶች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡-

| የሥራ ቡድን እና እየተሰራበት ያለ ጉዳይ | ሥራው ያለበት ደረጃ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ዳሰሳ ጥናት | የሕግ ማርቀቅ | ሕዝባዊ ምክክር | ሕግ የማውጣት | የአፈጻጸም ድጋፍ |
| **1. የበጎ አድራጎትና ማህበራት የሕግ ማእቀፍ የሥራ ቡድን** | | | | | |
| የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●● |
| **2. የፀረ-ሽብር ሕግ የሥራ ቡድን** | | | | | |
| የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●● |
| **3. የሚዲያ ሕግ ማዕቀፍ የሥራ ቡድን** | | | | | |
| የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●● | |
| የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | | |
| የመረጃ ነፃነትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | | |
| **4. የዴሞክራሲያዊ ተቋማት ጉዳዮች የሥራ ቡድን** | | | | | |
| ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን መልሶ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●● |
| የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●● |
| ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | |
| እንባ ጠባቂ ተቋም ዳሰሳ ጥናት | ●●●●●●● | | | | |
| የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ዳሰሳ ጥናት | ● | | | | |
| **5. የሕግ ዝግጅትና የአስተዳደር ሕግ ጉዳዮች የሥራ ቡድን** | | | | | |
| የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●● |
| የፌዴራል ሕግ ዝግጅትና የማውጣት ሂደት | ● | | | | |
| **6. የወንጀል ፍትህ ጉዳዮች የሥራ ቡድን** | | | | | |
| የወንጀል ፍትህ ስራዓት ሃገራዊ የዳሰሳ ጥናት | ●●●●●● | | | | |
| የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●● | |
| የፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅ | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●● |

[1] ለዋቢነት የሚከተሉትን ይመለከቷል - NYU and Pathfinders International, Ethiopia Country Report (Nov. 2019); Special Rapporteur on the promotion and protection of the right to freedom of opinion and expression, Visit to Ethiopia, End of mission statement (December 2019); David Kaye, Twitter Engagements (Dec. 11, 2019) https://twitter.com/davidakaye/status/1204828078871998470.

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 7. የንግድና ፍትሀ-ብሄር ህጎች የሥራ ቡድን | | | | | |
| የንግድ ሕግ | ●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●●●●● | ●●●● | |
| የገንዘብ አገልግሎቶች ሕግ | ●●● | | | | |
| 8. የጠበቆች/የሕግ ባለሙያዎች የሕግ ማእቀፍ የሥራ ቡድን | | | | | |
| የጥብቅና ሙያ አስተዳደር አዋጅ | ●●●●●● | ●●●●●●● | ●●● | | |
| 9. የመሰብሰብ እና ተቃውሞ የማድረግ መብት የሥራ ቡድን | | | | | |
| የመሰብሰብ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና አቤቱታ የማቅረብ አዋጅ | ●●●●●● | ●●●●●●● | ●● | | |
| 10. የመዘዋወር ነፃነት የሥራ ቡድን | | | | | |
| የመንቀሳቀስ መብት ዳሰሳ ጥናት | ●●●● | | | | |

**የአባላት ምልመላ ሂደት ያሉ የሥራ ቡድኖች**

11. ዘላቂ የሕግና ፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ የሥራ ቡድን
12. የሰብዓዊ መብት ሕጎችና ተቋማት መዋቅር የሥራ ቡድን
13. የዓለም አቀፍ የግለሰብ /የሕጎች ግጭት/ ህግ (conflict of laws ወይም private international law) የሥራ ቡድን
14. የሕግ ሥልጠና እና ትምህርት የሥራ ቡድን

| ደረጃ | ዝርዝር | ድምር |
|---|---|---|
| የተለያዩ የአፈጻጸም ወይም የአፈጻጸም ዝግጅቶች ድጋፍ የተካሄዱባቸው | ❶ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ፣ ❷ የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ፣ ❸ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን መልሶ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ፣ የምርጫ፣ ❹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ፣ ❺ የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ፣ ❻ የፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅ። | 5 |
| ፓርላማ ቀርበው የጸደቁ ሕጎች | ❶ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁ. 1113/2011)፣ ❷ የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ (አዋጅ ቁ. 1176/2012)፣ ❸ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን መልሶ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ (አዋጅ ቁ. 1162/2011)፣ ❹ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ (አዋጅ ቁ. 1133/2011)፣ ❺ የፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅ (አዋጅ ቁ. 1174/2012)፣ ❻ የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ (አዋጅ ቁ. 1183/2012)፣ ❼ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ። | 7 |
| በሕግ የማውጣጥ ሂደት ደርሰው በጠቅላይ ዐ/ሕግ፣ በሚኒስቴሮች ወይም በተወካዮች ም/ቤት እጅ ያሉ | ❶ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ፣ ❷ የመረጃ ነፃነትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ፣ ❸ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣ ❹ የንግድ ሕግ። | 4 |
| ሕዝባዊ ምክክር ሂደት ውስጥ ያሉ | ❶ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ፣ ❷ የመሰብሰብ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና አቤቱታ የማቅረብ አዋጅ። | 2 |
| ከጊዜ እጥረት አኳያ በቋሚ የሕግ ማሻሻያ ጠቋም ቢሰሩ የሚመረጥ | ❶ የፍትሀ-ብሄር ሕግ፣ ❷ ማጓጓዝን ወይም ማመላለስን የሚመለከት ሕግ፣ ❸ የሲቪል ምዝገባ ሥርዓት ሕግ። | 3 |
| በጠ/ዐ/ሕግ ተቀባይነት ያላገኙ | ❶ የጥብቅና ሙያ አስተዳደር ሕግ። | 1 |
| በመጀመር ያሉ ወይም በቅርቡ የሚጀመሩ[2] | ❶ የዓለም አቀፍ የግለሰብ /የሕጎች ግጭት/ ሕግ፣ ❷ የገንዘብ አገልግሎቶች ሕግ፣ ❸ የመንቀሳቀስ መብት፣ ❹ ሌላ የሰብዓዊ መብት ተቋማት መዋቅር ጋር የሚያያዙ የተለያዩ ሕግ ማሻሻያዎች። | 4 - 6 |
| | **ጠቅላላ የረቂቅ ሕጎች ድምር** | **26 – 28** |

[2] ሕግ የማውጣት አስፈላጂነት የሚወሰነው የጥናት ቡድኖች በሚያቀርቡት የውሳኔ ሃሳብ ተንተርሶ አማካሪ ጉባኤው በሚሰጠው ምክር መሰረት በመሆኑ የጥናት ቡድኖቹ የዳሰሳ ጥናት ሳይጠናቀቅ በቀጣይነት የሚሰሩ ረቂቆች ቁጥርን በሚመለከት እርግጠኛ ትንበያ ማድረግ አይቻልም።

## 4. በጉባኤው ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተሰጡ መፍትሄዎች

አማካሪ ጉባኤው ስራ በሚጀምርበት ወቅት ከነበሩ ችግሮች አንዱ የአማካሪ ጉባኤው ስራውን የሚያከናውንበት በጀት፣ ቋሚ ሰራተኞች፣ እንዲሁም የተሟላ የስራ ቦታ ወይም ቁሳቁሶች አለመኖር ነበር። ይህም በአማካሪ ጉባኤው አባላት፣ የሥራ ቡድኖች አባላት፣ እንዲሁም ጽ/ቤቱ ስብሰባ ለማድርግና ስራውን በአግባቡ ለመምራት እክል ፈጥሮ የነበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የአማካሪ ጉባኤውን ስራ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወጪዎችን በግላቸው ለመሸፈን ተገደው ነበር። እነዚህ ተግዳሮቶች ሙሉ በሙሉ ተቀርፈዋል የሚባልበት ደረጃ ባይደረስም የአማካሪ ጉባኤው የሁለተኛ ዓመት ከቁስና መዋለንዋይ አቅርቦት አንጻር ከፍተኛ መሻሻል የታየበት ነበር። እነዚህን ችግሮች ለማቃለል የጠቅላይ አቃቤ ህግ እና የአማካሪ ጉባኤው ጽ/ቤት ድጋፍ በማፈላልግ ቢሮና አሥፈላጊ ቁሳቁሶችን ማሟላት ችሏል። በቋሚነት ለሚሰሩ የጽ/ቤት ሠራተኞችም የአማካሪ ጉባኤው የስራ ዘመን እስከሚያበቃበት ጊዜ ድረስ በቂ ደሞዝ ለመክፈልና ኮምፒዩተሮችን ለማቅርብ ድጋፍ ተገኝቷል።

ሌላው አማካሪ ጉባኤው የገጠመው ተግዳሮት በዋናንት ከሚከተለው በጎ ፈቃደኝነት ላይ መሰረት ባደርገው የስራ ሞዴሉ ጋር የተያያዘ ነው። ምንም እንኳ ሥራው በበጎ ፈቃደኞች መሰራቱ በርካታ ጥቅሞች ቢኖሩትም የራሱ የሆኑ ውስንነቶችም ነበሩበት። ከነዚህም መካከል ስራዎችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ለማጠናቀቅ አለመቻል እና አልፎ አልፎ ከስራው ብዛት አንጻር የመዳከም አዝማምያዎች ይጠቀሳሉ። ይህን ችግር ለማቃለል ጠቅላይ አቃቤ ህግና የአማካሪ ጉባኤው ጽ/ቤት ድጋፍ በማፈላልግ የበጎ ፈቃደኞችን ሥራ የሚያግዙ የተወሰኑ አማካሪዎችን /consultants/ በመቅጠር የስራ ጫናውን ለመቀነስ እንዲሁም የሥራ የጊዜ ሰሌዳውን የተሻለ ፍጥነትና ተገማችነት እንዲኖረው ለማድረግ ተችሏል።

በሶስተኛ ደረጃ አማካሪ ጉባኤውን ያጋጠመው ችግር ከጠቅላይ አቃቤ ህግ ማርቀቅ ዳይሬቶሬት መሃል የነበረው መጠነኛ ክፍተት ነው። ምንም እንኳ ሁለቱ ተቋማት ተናበውና ተደጋግፈው ለተመሳሳይ አላማ በጋራ በመስራት ላይ ቢሆኑም የሁለቱ ተቋማት ስራ የሚመጋገብበት መደበኛ የሆነ አሰራር አለመዘርጋቱ የሚና መደራረብ፣ የጥረት ማባዛትና ብክነት፣ እንዲሁም የፖሊሲ ምክንያታቸው ግልጽ ያልሆኑ የስራ ውጤቶች አለመናበብ ተከስተዋል። የተነሱትን አለመናበቦች ለመፍታት ተደጋጋሚ ጥረት ቢደረግም በኮቪድ ወረሽኝ መከሰት እና በዚህ ጊዜ ውስጥ በጠ/ዐ/ሕግ መሪዎች የነበረው ከአንድ በላይ የመተካካት ሂደት ምክንያት በቀላሉ እልባት ሊያገኙ አልቻሉም። እነዚህን ተግዳሮቶች በጠቅላይ አቃቤ ህግ መ/ቤት መሪዎች እና በማርቀቅ ዳይሬቶሬት አባላት እንዲሁም ከአማካሪ ጉባኤው የተለያዩ አካላት ጋር ውይይት በማድርግ በመጀመርያ የተነሱ ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ በቀጣይነትም መዋቅራዊ በሆነ ሁኔታ ለመፈታት ተሞክሯል። በተመሳሳይ አማካሪ ጉባኤው ከተለያዩ አማካሪ ጉባኤው ከበርካታ አጋዥ ተቋማት (partner institutions) እና ጉባኤው የሚያጠናቸው ወይም ህግ የሚያረቅባቸው ፍሬ ነገሮችን የሚመለከቱ የመንግስት አካላት ጋር ጠንካራና ውጤታማ የስራ ግንኙኝነት አለው። ጠቅላይ አቃቤ ሕግ መስርያ ቤት አካላትና መሪዎች እነዚህ ግንኙነቶች የተሳለጡና ውጤታማ እንዲሆኑ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሲሆን በጠቅላይ አቃቤ ሕግ እና አማካሪ ጉባኤው በተዘረጉ አሰራሮች/መዋቅሮች ውስጥ መንቀሳቀስ ያልቻሉ አጋዥ ተቋማትን የመተካት ጥረትም በውጤታማነት ተጠናቋል።

በመጨረሻም በሀገራችን የኮሮና ቫይርስ መከሰቱ በአማካሪ ጉባኤው ስራ ላይ የራሱን መጥፎ ተጽእኖ ፈጥሮአል። ለዚህም መንስኤ የሆነው የአማካሪ ጉባኤው አብዛኛው ሥራ በቡድን የሚሰራና መሰባብስብን የሚፈልግ በመሆኑ ነው። ይህን ተግዳሮት ለመቋቋም የአማካሪ ጉባኤው ጽ/ቤት ቋሚ ሰራተኞች ቢሮ ሳይገቡ በበይነመረብ የሚሰሩበትን ሁኔታ ያመቻቸ ሲሆን የስራ ቡድን አባላትና ጉባኤውን ጨምሮ በበይነመረብ ስብሰባ የሚያካሄዱበትንና የትብብር ስራ የሚሰሩበት ሁናቴ አሰናድቷል።

በተጨማሪም የጽ/ቤቱ አባላት፣ የአማካሪ ጉባኤው የስራ ቡድኖችና ጉባኤው በአካል በሚሰባሰቡበት ጊዜ የጤና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የሚተገበር የ “COVID Guideline” ያዘጋጀ ሲሆን ወርርሽኙ በመከላከል የአማካሪ ጉባኤውን ሥራ ውጤትታማ ለማድርግ የሚያስችሉ መመሪያዎችን የያዘ ነው። ይህም Guideline በአማካሪ ጉባኤው ከፀደቀ በኋላ ከአማካሪ ጉባኤው ጋር በተያያዙ ሥራዎች በመመሪያነት የሚያገለግል ይሆናል።

## 5. የጉባኤው የሥራ ቡድኖችና የጽ/ቤቱ አባላት እና ሌላ በጎ ፈቃደኞች ዝርዝር

“” = የሥራ ቡድን አስተባባሪ

**የአማካሪ ጉባኤው አባላት**

1. ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ (የጉባኤው ሰብሳቢ)
2. ፕሮፌሰር ዛካሪያስ ቀነዓ
3. ዶ/ር ዘውድነህ ሃይሌ
4. አቶ ታምሩ ወንድማገኙሁ
5. አቶ ታደለ ነጊሾ
6. ወ/ሪት መሰረት ስዩም
7. ወ/ሮ ሊሻን ወልደመድህን
8. አቶ ሊቁ ወርቁ
9. አቶ ደበበ ሃይለገብርኤል
10. አቶ ቸርነት ወርደፋ
11. አቶ አሊ መሃመድ አሊ

**የአማካሪ ጉባኤው አባል የነበሩ**

12. ክብርት ወ/ሮ መአዛ አሸናፊ
13. ዶ/ር አበራ ደገፋ
14. ዶ/ር ጌታሁን ካሳ
15. ወ/ሪት ብሌን ሳህሉ
16. ወ/ሮ ሰምሃል ጌታቸው
17. አቶ ቁምላቸው ዳኘ

**የጽ/ቤቱ አባላት**

18. ዶ/ር አባድር መሀመድ (የጽ/ቤቱ ሃላፊ)
19. ዶ/ር ፀጋ አንዱዓለም (የጽ/ቤቱ ምክትል ሃላፊ)
20. አቶ አብዱላጢፍ ኢድሪስ (የጽ/ቤቱ የቀድሞ ምክትል ሃላፊ)
21. ወ/ሮ ገላኔ ጉሬ
22. ወ/ሮ ህሊና መኮንን
23. ወ/ሪት ቤተልሄም አብርሃም
24. ወ/ሪት ቃልኪዳን ምስጋናዉ
25. ወ/ሪት ረድኤት ባዬ
26. አቶ ከፋለ አስቻለ
27. አቶ ፋሲካ አለሙ
28. አቶ አዲ ደቀቦ ዳሌ
29. አቶ ዳኛቸው ጺጋዬ

**የበጎ አድራጎትና ማህበራት የሕግ ማእቀፍ የሥራ ቡድን**

30. አቶ ደበበ ሃይለገብርኤል
31. ዶ/ር ታደሰ ካሳ
32. ወ/ሮ ብሌን አስራት
33. ወ/ሮ ሜሮን አራጋ
34. አቶ አብዱላቲፍ ከድር
35. አቶ አበበ ፊጤ
36. አቶ ቁምላቸው ዳኜ
37. አቶ ወንጌል አባተ
38. አቶ ኪነጥበብ አረጋ

**የፀረ-ሽብር ሕግ የሥራ ቡድን**

39. ዶ/ር ጌዲዎን ጢሞቲዎስ
40. ዶ/ር ወንድወሰን ደምሴ
41. ዶ/ር አስመላሽ ዮሃንስ
42. አቶ አበበ አሳመረ
43. ው/ሪ ብሌን ሳህሉ
44. አቶ አምሃ መኮንን
45. አቶ በላይሁን ይርጋ
46. ወ/ሪ አመርቲ ሰለሞን
47. አቶ ሀሩይ በላይ
48. አቶ ቁምላቸው ዳኜ
49. አቶ ደሞዝ አማን
50. አቶ አዲ ደቀቦ

**የሚዲያ ሕግ ማዕቀፍ የሥራ ቡድን**

51. አቶ ሰለሞን ጎሹ
52. ዶ/ር መሰንበት አሰፋ
53. ዶ/ር ያሬድ መንግሥቱ
54. ወ/ሮ ቤቴልሄም ነጋሽ
55. አቶ ሃሌሉያ ሉሌ
56. ወ/ሪት ሃና ቤታቸው
57. አቶ ምስጋናው ሙሉጌታ
58. አቶ ሙሉጌታ አረጋዊ
59. አቶ መስፍን ነጋሽ
60. አቶ ዲባባ አመንሲሳ
61. አቶ ውብሸት ታዬ
62. አቶ ታዬ በላቸው
63. አቶ ታምራት ገ/ጊዮርጊስ
64. አቶ ኤልሻዳይ ነጋሽ
65. አቶ ሄኖክ ሰማዝገር
66. ወ/ሪት ማስተዋለዋል ተረፈ
67. ወ/ሪት ብርሃን ታየ

**የጠበቆች/የሕግ ባለሙያዎች የሕግ ማእቀፍ የሥራ ቡድን**

68. አቶ ማንያዉቃል መኮንን
69. ዶ/ር ሙሉጌታ መንግሥት
70. አቶ መስፍን ታፈሰ
71. አቶ ቴድሮስ ምህረት
72. አቶ ምህረተአብ ልኡል
73. አቶ አበራ ሃይለማሪያም
74. አቶ ፈቃዱ (ጠቅላይ ኣቃቤ ሕግ)

**የሕግ ዝግጅትና የአስተዳደር ሕግ ጉዳዮች የሥራ ቡድን**

75. ዶ/ር መሀሪ ረዳኢ
76. ዶ/ር ሰለሞን አባይ
77. ዶ/ር ዮናስ ቢርመታ
78. ዶ/ር ደመላሽ ረታ
79. አቶ አምሳሉ ባዬ
80. አቶ ወንድምአገኝ ገ/ስላሴ
81. አቶ ስለሺ ቀፀላ
82. አቶ ገ/አምላክ ገ/ጊዮርጊስ
83. ወ/ሮ ዜናዬ ታደሰ
84. አቶ ታፈሰ ይርጋ
85. አቶ መስፍን ለማ
86. አቶ አብርሃም ዮሃንስ
87. አቶ ሚኒሊክ አሰፋ

**የወንጀል ፍትህ ጉዳዮች የሥራ ቡድን**

88. ዶ/ር ሙራዱ አብዶ
89. ዶ/ር አለሙ ምህረቱ
90. ዶ/ር ማርሸት ታደሰ
91. ደ/ር ዳኛቸው አሠፋ
92. ዶ/ር ወንድማኝ ታደሰ
93. ዶ/ር መሠረት
94. ዶ/ር ስሜነህ ኪሮስ
95. አቶ ወርቁ ያዜ
96. አቶ ሽብሩ በለጠ
97. ወ/ሮ ትደነቅያለሽ ተስፋ
98. ወ/ት ቤዛ ንጉሴ
99. አቶ እዮብ አዋሽ
100. አቶ ኑሩ ሰዒድ
101. አቶ ዮሴፍ አእምሮ
102. አቶ ዳንኤል አረጋዊ
103. አቶ አብረሃም አያሌዉ
104. አቶ ቸርነት ሆርዶፋ
105. ኮ/ር በፈቃዱ ቶሌራ
106. አቶ ያለለት ተሾመ
107. አቶ አብዱልቃድር መሀመድ
108. አክሊለ ሰለሞን
109. ወ/ሮ እየሩሳሌም ተሾመ
110. አቶ ቀለምወርቅ ሚዴቅሳ

**የዴሞክራሲያዊ ተቋማት ጉዳዮች የሥራ ቡድን**

111. ዶ/ር ጌታቸው አሰፋ
112. ፕ/ር ካሳሁን ብርሃኑ
113. ፕ/ር ተሰማ ተኣ
114. ፕ/ር መረራ ጉዲና
115. ዶ/ር አሰፋ ፍሰሃ
116. ዶ/ር ጌታሁን ካሣ
117. ዶ/ር እመዛት ሃይሉ
118. ዶ/ር ሲሳይ አለማሁ
119. ዶ/ር መሀመድ አብዶ
120. ዶ/ር ዮናታን ተስፋዬ
121. ዶ/ር ብርሀነመስቀል
122. አበበ ሰኚ
123. አቶ ብስራት መኮንን
124. አቶ መታሠቢያ ሃይሉ
125. ሶሊያና ሽመልስ
126. ወ/ት ብዙወርቅ ከተተ
127. ወ/ሮ አንቺነሽ ሽፈራው
128. ማከዳ ጌታቸዉ
129. አቶ አብዲ ጅብሪል
130. አቶ ምትኩ መኮነን
131. አቶ አይተነዉ ደበበ
132. አቶ ያደታ ግዛዉ
133. አቶ የማነ ካሳ

**የንግድና ፍትሀ-ብሄር ህጎች የሥራ ቡድን**

134. አቶ እስራኤል ተክሌ
135. ፕ/ር ዘካሪያስ ቀንኣ
136. ዶ/ር ታደሰ ሌንጮ
137. አቶ ሰለሞን እምሩ
138. አቶ ስዩም ዩሃንስ
139. አቶ ተስፋዬ ሀ/ማርያም
140. ወ/ት ምንትዋብ አፈወርቅ
141. ወ/ት ማርታ በለጠ
142. አቶ ፍቃዱ ጴጥሮስ
143. አቶ አማን አሰፋ
144. አቶ በሀካል አባተ
145. አቶ ኤፍሬም ሀይለማሪያም
146. ወ/ት ማህሌት ካሳ
147. አቶ ገዙ አየለ
148. አቶ ጄቱ ኤዶሳ
149. አቶ ስንታየሁ ዘለቀ
150. አቶ አሰፋ አሊ
151. አቶ ዮናስ መላኩ
152. አቶ በላይ ከበደ
153. አቶ ፀሀይ ዋዳ
154. ወ/ሮ ትርሀስ ገብረ እግዚያብሄር
155. አቶ ምትኩ ማዳ
156. ወ/ሮ ራህዋ መብራህቱ
157. አቶ በላይሁን ይርጋ
158. አቶ አባት አበበ
159. አቶ ይነበብ ደርሰህ

**የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነት ህግ ማሻሻያ የሥራ ቡድን**

160. ዶ/ር አብዲ ጅብሪል
161. ዶ/ር ቃልኪዳን ነጋሽ
162. ዶ/ር ዮናስ ተስፋ
163. ዶ/ር ሚዛኔ አባተ
164. ዶ/ር ደመላሽ ሽፈራዉ
165. አቶ ባንታየሁ ደምሌ
166. አቶ ዉብሸት ካሳዉ

**የመንቀሳቀስ መብት የስራ ቡድን**

167. አቶ ዮናስ ግርማ
168. አቶ አቤል ቸርነት
169. አቶ ሄኖክ አሻግሬ
170. አቶ አወት ሀይለዝጊ
171. አቶ ሞላልኝ አስማረ
172. አቶ ብሩክ ደረጀ
173. አቶ አየለ ዉብሸት

**የሥራ ቡድን ወይም የጽ/ቤቱ ሙሉ አባል ሳይሆኑ በበጎ ፈቃደኝነት ያገለገሉ**

174. ዶ/ር ዘላለም ሞገሴ
175. ዶ/ር ህሩይ ውቤ
176. ዶ/ር አደም ካሴ አበበ
177. አቶ ሰይፈ አያሌው
178. ወ/ሪት ኤድና አለማየሁ
179. ወ/ሪት ማስተዋል ተረፈ
180. አቶ ሚኒሊክ አሰፋ
181. አቶ ዮሃንስ ተስፋዬ
182. ወ/ሪት ሃና ቴይለር
183. ወ/ሪት ጀኔፈር ሂል

184. ወ/ሪት ዘመን መኮንን

**እጩ አባላት**

**የአለም አቀፍ የግለሰቦች ህግ የሥራ ቡድን**

185. ፕሮፌሰር/አምባሳደር ኢብራሂም ኢድሪስ
186. ዶ/ር ሳሙኤል ተሻለ ደርቤ
187. አቶ አርኣያ ከበደ
188. እጩ ዶ/ር ሱልጣን ቃሲም ገና
189. አቶ አበበ አበባየሁ
190. አቶ እዩኤል በሀይሉ ወ/ማሪያም

**የህግና ፍትህ ማሻሻያዎች ዘላቂነት የሥራ ቡድን**

191. ዶ/ር ሙሉጌታ መንግስት
192. አቶ አለባቸዉ ብርሀኑ
193. መሳይ መስቀሌ ጺጋዬ
194. አቶ ዘካሪያስ ኤርኮላ
195. አቶ መስፍን እሸቱ
196. አቶ ባንታየሁ ደምሌ
197. አቶ በላይሁን ይርጋ
198. ሀናን አበበ

**የህግ ትምህርት የሥራ ቡድን**

199. ዶ/ር ደጀኔ ግርማ
200. ዶ/ር ሙራዱ አብዶ
201. ዶ/ር ብሩክ ሀይሌ ገረዮ
202. ዶ/ር አብዱልማሊክ አቡበከር አህመድ
203. ዶ/ር ቃልኪዳን ነጋሽ ኦብሴ
204. አቶ እዮብ አዋሽ

**የሰብዓዊ መብት ሕጎችና ተቋማት መዋቅር የሥራ ቡድን**

205. ዶ/ር አብዲ ጅብሪል
206. ዶ/ር መቅደስ ታደለ
207. ዶ/ር አደም ካሴ
208. ዶ/ር ዘላለም ተፈራ
209. ዶ/ር ግርማቸዉ አለሙ
210. ዶ/ር ሚዛኔ አባተ ታደሰ
211. ዶ/ር ታከለ ሰቦቃ
212. አመርቲ ሰለሞን
213. ቃልኪዳን አበራ
214. አቶ ሳሙእል ጥላሁን
215. የምስራች ለገሰ